የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ—ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. 42
ADDIS ABABA–6[th] July, 2001

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፪ ዓ.ም
ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር (ማሻሻያ) ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ........... ገጽ·

## CONTENTS

Proclamation No. 252/2001
Agreement Amending the International Development Association Credit Agreement for Financing the National Fertilizer Sector Project Ratification Proclamation ............................................. Page

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፪/፲፱፻፺፫
### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ማሻሻያ ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· ፹፪ ሚሊዮን ፱፻ ሺ (ሰማንያ ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ኤስ·ዲ·አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ ሴፕቴምበር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ የተፈረመ በመሆኑ ፤

ለፕሮጀክቱ ድጋፍ የሚውል ተጨማሪ ኤስ·ዲ·አር ፴፬ ሚሊዮን ፯፻ ሺ (ሠላሳ አራት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሺ ኤስ·ዲ·አር) ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር በብድር ለማግኘት የሚያስችል የማሻሻያ ስምምነት እ·ኤ·አ· ጁላይ ፲፰ ቀን ፪ ሺ ፩ በዋሽንግተን ዲ·ሲ ስለተፈረመ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው ፤

ይህንኑ የማሻሻያ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩ አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የማዳበሪያ ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር (ማሻሻያ) ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፶፪/፲፱፻፺፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 252/2001
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT AMENDING THE CREDIT AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Credit Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Credit amount of SDR 82,900,000 (eighty two million nine hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the National Fertilizer Project was signed on the 29[th] day of September 1995;

WHEREAS, an Amending Agreement stipulating that the International Development Association provide an additional loan amount of SDR 34,700,000 (thirty four million seven hundred thousaand Special Drawing Rights) in support of the Project has been signed in Washington D.C. on the 18[th] day of July, 2001;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Amending Agreement at its session held on the 6[th] day of July, 2001.

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Agreement Amending the International Development Association Credit Agreement for Financing the National Fertilizer Sector Project Ratification Proclamation No. 252/2001."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ “የማሻሻያ ስምምነት” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ጁላይ ፲፰ ቀን ፪ሺ ፩ በዋሽንግተን ዲ.ሲ. የተፈረመው ቁጥር ፪ሺ፯፻፵-፩-ኢ.ቲ. የብድር (ማሻሻያ) ስምምነት ነው።

፫. የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በማሻሻያው ስምምነት የተገኘውን ኤስ.ዲ.አር. ፴፬ ሚሊዮን ፯፻ ሺ (ሠላሳ አራት ሚሊዮን ሰባት ሺ ኤስ.ዲ.አር) በማሻሻያ ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም.

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Amending the Agreement" means the Agreement Amending Development Credit Agreement No. 2740-1-ET signed on the 18th day of July, 2001 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of SDR 34,700,000 (thirty four million seven hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Amending Agreement.

4. *Effective Date*

*This Proclamation shall enter into force as of the 6th day of July, 2001.*

*Done at Addis Ababa, this 6th day of July, 2001.*

*NEGASO GIDADA (DR.)*

*PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE